# ወዮላችሁ!

(ከማህሉ በቀለ - ቶሮንቶ)

ህዝቡን በዘር ከፍላችሁ
እንዳይጮህ አፉን ዘግታችሁ
እንዳይበላ መሬቱን ሸጣችሁ
ባለአገሩን ጠልታችሁ ንቃችሁ
የት ትገቡ ይሆን፣ እንዳው ወዮላችሁ
የለውጡ ሱናሚ፣ ሲደርስ ከበራችሁ፡፡

በስልጣን መባለግ፣ በሙስና መዝፈቅ
በድሆች ምድር ላይ፣ በሀብት መጨማለቅ
የትም አያደርስም፣ ቀኑ ሊመጣ ነው
የተቀበረው ቦንብ፣ ያው ሊፈነዳ ነው፡፡

እኔ ብቻ ልግዛ፣ ሆነና ነገሩ
የወያኔ ሥርዓት፣ የዘር መዋቅሩ
በእኩልነት ስም፣ አበሻን ከፋፍለው
በክልል በጎሳ፣ በነገድ ሸንሽነው
እነሱ ዙፋን ላይ፣ ጉብ ቂንጥጥ ብለው
ጮማው ሲዘለዘል፣ ውስኪው ሲንቆረቆር
የቅንጦቱ ዕቃ፣ በፎርም ሲደረደር
ስትስቁ ስታብዱ፣ ስትመዣረጡ
ስትፍነከነኩ፣ እንደ ልጅ ስትቀብጡ
እንዲያው ወዮላችሁ፣ የት ትገቡ ይሆን
ያ ቀን የመጣ ለት፣ ህዝቡ ገዥ ሲሆን፡፡

በቱኒስያ ምድር፣ እሳት ተጫረ አሉ
በግብፆችም ምድር፣ እሳት ነደደ አሉ
በየመን በሊቢያ፣ እሳት ጨሷል አሉ
የኢትዮጵያ እሳት፣ ግን ተዳፍኗል ከሰሉ
እስኪ እናንድደው፣ እፍ እፍ በሉ፡፡

ለአምባገነን መንግሥት፣ ህዝቡን ላልወከለ
መገዛት አንመርጥም፣ ነፃነት እያለ
ባንድነት ከቆምን፣ ትግሉ ከቀጠለ
የወያኔም ውድቀት፣ አድሮ ይታይ የለ?

ታላቋን እመቤት፤ ቡትቶ አልብሰው
ለማኝ እርሀብተኛ፤ በሽተኛ አርገው
ክብርና ኩራቷን፤ አሽቀንጥረው ጥለው
ጀግና ታጋዮቿን፤ አስረውና ገድለው
ለጊዜው ቢመስሉ፤ ብልጥና ሀይለኛ
መውደቃቸው አይቀር፤ ስንነሳ እኛ፡፡

አቤት ጭካኔያችሁ፤ ተንኮል ውሽታችሁ
ክፋት ቅጥፈታችሁ፤ ኋላ መቅረታችሁ
ለራስ መቆማችሁ፤ አገር መናቃችሁ
ታሪክ ያልገባችሁ፤ ለዘር የቆማችሁ
ጠባብ የሆናችሁ፤ እንዳው ወዮላችሁ
አሳፋሪ ናችሁ፤ ታሳዝናላችሁ፡፡

ነፃ አውጭ ነን ስትሉ፤ ትንሽ የማታፍሩ
የማይደግፋችሁን፤ ስትገሉ ስታስሩ
የግል ጦር ሠራዊት፤ የምታቋቁሙ
የአበሻን ንብረት፤ በጉልበት የምትቀሙ
ስለ ሰብዓዊ መብት፤ የማትጨነቁ
በንፁሀን ህዝብ ደም፤ ስትጨማለቁ
ፋሽስት መሆናችሁ፤ ተጋለጠ ሐቁ፡፡

በግፍ አገዛዝ ወደር የሌላችሁ፤ ሻምፒዮን የሆናችሁ
ያች ቀን ስትመጣ፤ እንዲያው ወዮላችሁ
መቸም ሰው አትሆኑም፤ ታሳዝናላችሁ፡፡
እንዲያው ቢገባችሁ፤ ይህን ልንገራችሁ
ኢትዮጵያን በጉልበት፤ በሀይል መግዛታችሁ
ጊዜ አዳልቶ ነው፤ አይደል በስራችሁ፡፡

ጊዜ የሰጠው ቅል፤ ድንጋይን ይሰብራል
ቅሉም ቀኑ ሲደርስ፤ በአፈር ይበላል፡፡

አምባገነን ሁላ፤ እንዲያው ወዮላችሁ
ያች ቀን ስትመጣ፤ የት ይሆን መግቢያችሁ
ማሰብ ከቻላችሁ፤ ህሊና ካላችሁ
ታሪቁ ከህዝቡ፤ ቅጥፈት ይቅርባችሁ
አበሻ መሀሪ ነው፤ ታሪክ ቢገባችሁ♦